## የኢየሱስ ምልጃ እና የኦርቶዶክሳውያን ስህተት

የኢየሱስን ምልጃ በተመለከተ አንዳንድ ሰዎች በመካድ ሌሎቹ ደግሞ ባለመረዳት በክርስትና ውስጥ ያለውን ታላቅ ሚና ዋጋ አልባ ያደርጉታል ። የኢየሱስ መሞት በክርስትና እምነት ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ሲሆን ኢየሱስ ስለ እኛ ሞተ ብቻ ሳይሆን የኖረውንም ኑሮ ስለ እኛ ነው። ከሁለም በላይ ደግሞ ስለ እኛ ኖረ ፣ ስለእኛ ሞተ ከሚለውም በላይ ከሙታን ተነስቶ ስለ እኛ ነው በአባቱ ዘንድ ያለው የሚለው እጅግ የተዘነጋ እውነታ እንደሆነ አስባለሁ ። **— ሮሜ 5፥10 (አዲሱ መ.ት) ። "የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕርቅን ካገኘን በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም!"** በህይወቱ የሚለው ከትንሳኤው በኋላ ስላለው ህይወት ነው ። ኢየሱስ ኩመታን መነሳቱ እና እኛን ወክሎ በአባቱ ዘንድ መሆኑ ድህነታችንን በተመለከተ ለዋስትናችን መሰረታዊ ነገር እንደሆነ ይህ ክፍል ይጠቁመናል ።

### ምልጃን በተመለከተ የኦርቶዶክሳውያን ክህደት

ኢየሱስ ይማልዳል ሲባል ትልቅ ስህተት ሆኖ ሚታያቸው ኦርቶዶክሳውያን ወገኖች ጥቂት አይደሉም ። የሚያቀርቧቸው የራሳቸው ሙግቶች እና የመፅሐፍ ቅዱሳዊ የመከራከሪያ ምንባባትንም ይጠቅሳሉ። ኦርቶዶክሳዊያን ክርስቶስ በእዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ የማማለድ እና የሊቀ ክህነቱን አገልግሎት ፈፅሟል ይላሉ ። ለእዚህም እንደማስረጃ ሁለት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ይጠቀማሉ ። **— ዮሐንስ 17፥4 (አዲሱ መ.ት) ። "የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርሁህ"።** በዚህ ክፍል ኢየሱስ ስራውን የፈፀመ ከሆነ መሞቱ ለምን አስፈለገው ? ምክንያቱም ኢየሱስ የሰጠኸኝን ስራ ፈፀምኩ ሲል ገና እንዳልሞት ግልጽ ነው ። እንደውም ምድር ላይ የመጣበት ዋና ምክንያቱ ሞተ እንደሆነ ግልጽ ነው ። ስለዚህ እዚህ ጋር ከደቀመዛዙጋር የተያያዘ ነገር እንጂ ስለሁም የእግዚአብሔር ፈቃዶች መፈፀሙን እያወራ አይደለም ።

እንደ ኦርቶክሳዊያን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ፀለየ ፣ አማለደ ወይንም ያማልዳል ተብሎ ሊነገርለት አይገባም ። እንደውም በተገላቢጦሹ ከትንሳኤው በኋላ ፀሎትን እና ምልጃን የሚቀበል አምላክ ነው ይላሉ ። ኢየሱስ የፀሎትን እና የምልጃን አገልግሎቱን ለቅዱሳን መላዕክት ፣ ለቅድስት ድንግል ማርያም እና ለቅዱሳን ሰማዕታት ሰጥቷል ይላሉ ።

**– እዚህ ላይ የተወሰኑ የመከራከሪያ ነጥቦችን መልስ እንስጥበት**

1ኛ, ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ እና ካረገ በኋላ አይማልድም ?

መፅሐፍ ቅዱሳችን ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ እና ካረገ በኋላ እንደሚማልድ ይነግረናል ። ሮሜ 834 ላይ
**፦" የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ስለ እኛ ይማልዳል።"**

በእዚህ ክፍል ውስጥ የሞተው እና የተነሳው የሚሉ የግሪክ ግሶች በማያሻማ ሁኔታ **ኤሪስት** ወይንም የኃላፊ ጊዜ ግሶች ናቸው ። እንዲሁም ደግሞ በእግዚአብሔር ቀኝ መሆኑን እና ስለ እኛ የሚማልድ መሆኑን ደግሞ በ **present tense** ነው ያስቀመጠው ። ኢየሱስ ሞቶ ከሙታን ተነስቶ ወደሰማይ ባረገበት ጊዜና ጳውሎስ የሮሜን መልዕክት በጻፈበት ጊዜ መካከል የጊዜ Gap እንዳለ ግልጽ ነው ። ጳውሎስ አሁንም ኢየሱስ እየማለደ ነው እያለን ነው ። ከሙታን ተነስቶ አርጎም እንኳን እየማለደ ነው ይለናል ። ነገርግን የኢየሱስ የክህነት ስራ ምድራዊ እና ሰማያዊ ገጽታዎቹ የተለያዩ ቢሆኑም የአንድ ሙሉ ቤት የተለያዩ ክፍሎች አድርገን ልንወስድ እንችላለን ። ይህንን

ቀጥሎ ለማብራራት እሞክራለሁ ።

2ኛ, ያማልዳል የሚለውን ቃል ትርጉም ምን ማለት ነው?

ምልጃ የሚለው ቃል በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በግሪኩ **«ἐντυγχάνει»(ኢንቱግካኔ)** እና **«διότι»(ዲዮቲ)** በሚሉ ሁለት ቃላት ተገልጸዋል። በኢየሱስ የተደገረው ምልጃ በሁለቱም ተገልጾአል። ልዩነታቸው ምንድነው? ‹‹**ኢንቱግካኔ**›› የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉዋሜው ፦ ለአንድ አካል ወግኖ ወይም አንድን አካል ተቃውሞ የሚደረግ መጠይቅ ወይም ልመና ማለት አንችላለን(ሮሜ. 8፡27፣34 እና ዕብ 7፡25 ላይ :ለተቃውሞው (ሐዋ.25፡24 እና ሮሜ.11፡2 ማየት እችላለን። በየትኛውም የአዲስ ኪዳን ክፍል ከኢየሱስ የ33 ዓመት የምድር ቆይታ ወይም ከሞት ከመነሳቱ በፊት ከነበረው የሥራ ድርሻ ጋር በተገናኘ ኢንቱግካኔ የሚለው የግሪክ ቃል ጥቅም ላይ ሲውል አንመለከትም ።

**«ዲዮቲ››** የሚለው ቃል ደግሞ ትርጉዋሜው ደግሞ ጸሎት ወይም ልመና በሚለው ይፈታል። ይህም በጠቅላላው አንድ በእግዚአብሄር ህልውና የሚያምን ሰው የሚያደርገውን ጸሎት ይመለከታል። ለዚህ ሉቃ.1፡13 እና 1ጴጥ.3፡12 ማየት ይቻላል። ይሄንን ደግሞ በኢየሱስ የ33 ዓመት የምድር ቆይታ ላይ አንዴ ተጠቅሱዋል። ይህም በሉቃ.22፡32 ላይ ይገኛል። ከሞቱ በሁዋላ ግን ይህ ቃል አንድም ጊዜ ለኢየሱስ አልተጠቀሰም ።

እንግዲህ ከዚህ ማወቅ የምንችለው መጽሀፉ ‹‹**ዲዮቲ**›› የሚለውን ቃል ሲጠቀም በየትኛውም ቦታ አንድ በአጸደ-ሥጋ ያለ ሰው ለሌላ በአጸደ-ሥጋ ላለ ሰው ወደ እግዚአብሄር የሚያደርገው ጸሎት ነው ። ኢየሱስም በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ለእነጴጥሮስ ያደረገው ይሄንኑ ነው ። ስለዚህ ከሞት ቡዋላ እንዳለው አይነት ምልጃ አይደለም ። ይሄ የጸሎት ምልጃ በብዙ ክርስቲያኖች ሲደረግ የነበረና እስከጌታ መምጫ የሚደረግ ነው ።

መጽሀፉ ‹‹ኢንቱግካኔ›› የሚለውን ቃል ለኢየሱስ ሲጠቀም ጸሎት ያደርጋል ማለት ሳይሆን ይከራከራል፤ እንደ ጠበቃ ደግፎ ይሙዋገታል ማለት ነው። ይህንን ቃል መጽሀፉ ለሰው ሲጠቀመው ሁለት ጊዜ ሲሆን እሱም ተቃውሞ ለማሰማት የተደረገ ነው። ለመንፈስ ቅዱስም ይህንኑ ቃል ይጠቀማል። ይህም በጸሎት ጉዳይ የእግዚአብሄርን ፈቃድ መንፈስ ቅዱስ ስለሚያውቅ ክርስቲያኖች የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማወቅ ባልቻሉበት እና/ወይም ደካማ በሆኑበት ነገር ላይ የእግዚአብሄር ፈቃድ እንዲፈጸም ስለነሱ እንደነሱ ሆኖ ወደ አብ ይጸልያል።

የኢየሱስ ምልጃ ከመሞቱ በፊት እና በሁዋላ የተለያየ ነው?

ከሞቱ በፊት እንደማንኛውም ሰው ስለሚፈልገው ሰው ወደ እግዚአብሄር አብ ይጸልይ ነበር። ከሞቱ በኃላ ደግሞ አዲስ ምዕራፍ ነው ። ይህን ማለት

እንደ ዕብ.9:22 ገለጻ ደም ሳይፈስ ስርየት የለም። ስለዚህ እንደ ህጉ ለአብ የሚቀርብ ንጹህ መስዋዕት፤

እንዲሁም ፍጹም ሊቀ ካህናት ያስፈልግ ነበር። እንግዲ በመስቀል ላይ መስዋዕት የሆነው በግ ኢየሱስ

ነው። **— ኤፌሶን 5፥2 (አዲሱ መ.ት) ። “ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።”** የዕብራውያን ጸሃፊም ‹‹ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህንን(መስዋዕትን) አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድረጉዋል።›› በማለት ይደጋገም የነበረውን የመስዋዕት ስርዓት እንዳስቀረው ይናገራል። ከዚያም በሁዋላ ግን ይህን የፈሰሰውን የመስዋዕቱን ደም በጊዜው በኢየሩሳሌም በነበረችው ቅድስት ሳይሆን በሰማይ ወዳለችው ቅድስት የሚያስገባ ፍጹም ሊቀ ካህናት ተፈልጎ

ኖሮ አብ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ በመሃላ ሾመው ። የዕብራውያን ጸሃፊ ይህንን ሀሳብ ‹‹(በመከራው) ከተፈጸመም በሁዋላ በእግዚአብሄር ‹እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ነህ› ተብሎ ተጠራ›› በማለት ይገልጸዋል።

ሹመቱ የተነገረው ከጥንት ነው። ኢየሱስ በመከራው ሳይፈጽም ግን ሊቀ ካህናት ሊሆን አይችልም ነበር።በመከራ ሳያልፍ ሊቀካህናት ሊሆን የማይችልበት ምክኒያቱ እንዲያ ካልሆነ ለሀጢያተኞች የሚራራ ስለማይሆን ነው። ስለዚህም ጸሃፊው ‹‹ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ›› አለ። ባይሆን ኖሮ በኢየሩሳሌም ባለችው ቅድስት ገብቶ ደም መርጨት ነበረበት።ይህንን እንዳላደረገ ግን ግልጽ ነው። ጸሃፊው ይሄንንም ሲገልጽ ‹‹እንደ አሮንም በእግዚአብሄር ከተጠራ በቀር ክብሩን ለራሱ የሚወስድ ስለሌለ ክርስቶስ ሊቀካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም›› ሊቀካህናት እንዲሆን ያከበረው ግን ‹‹አንተ ልጄ ነህ›› ያለው አብ ነው ። መከራውን ከፈጸመ በሁዋላ በእርገቱ ወደ ቅድስት ገባ ። አሁን በዚያ እንደ ዮሐንስ አባባል ከቅድስት ሳይወጣ በአብ ዘንድ ስለ ክርስቲያኖች ጠበቃ የሆነው እሱ ነው። እንደ እብራዊያን ጸሃፊ ገለጻ ደግሞ በእግዚአብሄር ዘንድ ስለእኛ(ክርስቲያኖች) አሁን ይታይ(በዮሐንስ ጥብቅና የተባለው ነው) ዘንድ ወደ እርሱዋ(ቅድስት) ወደ ሰማይ ገባ። እንግዲህ እስከ ዳግም ምጽዓቱ ድረስ በቅድስት ይቆያል። ምን እያደረገ ስለክርስቲያኖች እየተከራከረ፣እየተሙዋገተ፣ጥብቅና እየቆመ

ነዋ። ጳውሎስም ሆነ የዕብራውያን ጸሃፊ ‹‹ኢንቱግካኔ›› የሚለውን ተጠቅመው ኢየሱስ ያማልዳል ብለዋል። ‹‹…ስለእኛ የሚማልደው…›› ‹‹ ስለ እነርሱ ሊያማልድ…›› እኛ እና እነርሱ ክርስቲያኖችን ስለሚወክል አንድ አይነት ነው። በእግዚአብሄር ቀኝ መቀመጡ ዳግም በመከራ ውስጥ እንደማያልፍ እና ስለሀጢያት መስዋዕት እንደማይሆን የሚያሳይ ነው። መስዋዕት መቀበሉንም ሆኖ ሙግቱን ስለማቆሙ አያሳይም ። መስዋዕቱ በአብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱንም ይኸው ያሳያል። **— ዕብራውያን 9፥24 (አዲሱ መ.ት) ። “ክርስቶስ የእውነተኛዪቱ ድንኳን ምሳሌ ወደ ሆነችውና በሰው እጅ ወደ ተሠራችው መቅደስ አልገባም፤ ነገር ግን አሁን ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት፣ ወደ እርሷ ወደ ሰማይ ገባ።”**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በ 2000 አ.ም ባሳተመችው የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይህ ጥቅስ እንደሚከተለው ተተርጉሟል ። **“ዘወትር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሊያድናቸው ይቻለዋል ፤ ለዘለዓለም ህያው ነውና ያስታርቃቸዋል ።”** ሮሜ 8:34 ላይም ስለ እኛ የሚማልደው የሚለውም ስለ እኛ የሚፈርደው ብለው ተርጉመውታል ።

በእዚህ በዕብራውያን መፅሐፍ ላይ ያስታርቃቸዋል ብለው የተረጎሙት የግሪክ ቃል **ኢንቱካኖ** የሚል ነው ። ይህ ቃል 5 የኢዲስ ኪዳን መፅሐፍ ላይ የምናገኘው ሲሆን 3ቱ ሮሜ ላይ ፣ አንዱ እዚሁ ዕብራውያን ላይና አንዱ ሐዋሪያት ስራ ላይ ይገኛል ። አንዱም ቦታ ማስታረቅ የሚል ትርጉም የለውም ። ማስታረቅ ለሚለው ቃል ሌላ የግሪክ ቃል አለ ። እርሱም **“ካታላስ”** የሚለው ነው ። ስለዚህ ቃሉን ባልተገባ መንገድ ለእራሳቸው አላማ ይተረጉሙታል ።

ኢየሱስ መስዕዋት ነው ስንል እና ለቀ ካህን ነው ስንል ምን እያልን እንደሆነ ከተብራራ የክርስቶስ ምልጃ ግልጽ ይሆንልናል ። በብሉይ ኪዳን የመቅደሱን አገልግሎት ከተመለከትን የእንስሳቶቹ ደም መፍሰስ ብቻውን በቂ አልነበረም ። የፈሰሰውን የእንስሳት ደም የሚያቀርብ ሊቀ ካህናት አስፈላጊ ነበር ። እንደዚሁ ኢየሱስ ደሙን ማፍሰሱ ብቻ ሳይሆን ደሙን ይዞ የሚቀርብ መሆኑም እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው ። ኢየሱስ በእጅ ወዳልተሰራችው ሰማያዊ መቅደስ ደሙን ይዞ ገቡቷል ። ይህን የክህነት ስራው ወይንም አገልግቱ እኛን ወክሎ ስለ እኛ የሚደረግ የምልጃ አገልግሎት ነው ።

**3ኛ, እርሱ እኮ አምላክ ነው ። ፀሎት ተቀባይ እንጂ ፀሎት አድራሽ አይደለም ። ፀሎትን ማድረስ የፍጡር ስራ ነው ለሚሉት መልስ እንስጥ ።**

ይህ የከበረው ጌታ አምላክ ሆኖ ሳለ እንዴት ስለ እኛ ይማልዳል? ይላሉ ። ለእዚህ መልሱ ቀላል ነው ። እነሱ እንደሚሉት ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ይፀልይ ፣ ይማልድ ነበር ። በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሲማልድ እና ሲፀልይ መቼ መለኮትነቱ ቀረ ? ሰው መሆኑ መለኮትነቱን የማያስቀር ከሆነ ይህንን ጥያቄ ሊያነሱ አይገባም ። ኢየሱስ እኮ መስዕዋትም ካህንም ነው እንላለን ፣ ኢየሱስ የበጎች እረኛ ደግሞም መግቢያ በሩም ነው እንላለን፣ ኢየሱስ የይሁዳ አንበሳ ደግሞም የአለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው ። አንድ ነገር መሆኑ ሌላ ነገር እንዳይሆን አላገደውም ። ኢየሱስ አምላክ ቢሆንም አብን ግን አይደለም።አብ እና ኢየሱስ ባህሪ መለኮትነታቸው እንጂ አካልነታቸው አንድ አይደለም። የአብ የስራ ድርሻ ከወልድ ይለያል። አብ መስዋዕት ተቀባይ ሲሆን ኢየሱስ ደግሞ አቅራቢ ነው። ኢየሱስ አማላጅ ሲሆን አብ ደግሞ ተማላጅ ነው።

ይህንን ስል አንድ ነገር ትዝ አለኝ ። አንድ የኦርቶዶክስ ቄስ በለቅሶ አጋጣሚ ተገናኝተን ስናወራ ኢየሱስ ካረገ በኋላ መለኮት ብቻ ነው ሰውነቱን ትቷል አለኝ ። በጣም የገረመኝ ደግሞ ለእዚህም ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው 2ኛ, ቆሮንቶስ 5 ላይ ያለውን ቃል ነው ። **— 2ኛ ቆሮ 5፥16“ስለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ፥ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።”** ይህ ሌሎች Translationsኦችን ያለማየት ችግር ነው ።

ከዚያ መለስ አድርጌ እና እኛስ አሁን በስጋ አይደለንም ማለት ነው ? አልኩት ። ምክንያቱም ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን ሰዎችንም **ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም** ነው የሚለው አልኩት ።

ሌላም ጥያቄ ጠየኩት ክርስቶስ እግዚአብሔር አምላኬ የሚለው በሰውነቱ ነው ወይንስ በመለኮትነቱ ነው ? ብዬ ጠየኩት። እሱም በሰውነቱ ነው አለኝ ። ራዕይ የተፃፈው ኢየሱስ ካረገ በኋላ ነው አይደል? ስለው አዎ አለኝ ። ራዕይ ላይ ድል ለነሳው በአምላኬ ዙፋን አምድ አስቀምጠዋለው ይላል ። ስለዚህ ኢየሱስ አሁንም እግዚአብሔርን አምላኬ ብሎ የሚጠራ ከሆነ ፍፀምም ሰው ነው ማለት ነው አልኩት ። ሙግታች ከእዚያ በላይ መቀጠል አልቻለም ።

የኢየሱስ ፍፁም ሰውነት ሳይነጣጠል ፣ ሳይደባለቅ ፣ ሳይዋዋጥ እና ሳይጠፋፋ ሁለቱ ባህሪ በአንድ አካል ውስጥ **ለዘለአለም** ይኖራሉ ። ፍፁም አማላክ መህኑ ሰውነቱን አላጠፋም ፣ ፍፁም ሰው መሆኑ ፍፁም አምላክ እንዳይሆን አልከለከለውም ።

**4ኛ, ኢየሱስ የፀሎትን እና የምልጃን አገልግሎቱን ለቅዱሳን መላዕክት ፣ ለቅድስት ድንግል ማርያም እና ለቅዱሳን ሰማዕታት አስተላልፏል ይላሉ?**

1ኛ, ኢየሱስ የምልጃ አከልግሎቱን እንዳስተላለፈው የሚገልጽ አንድም ማስረጃ የለም ።

2ኛ, ቅዱሳን ለሌሎች ቅዱሳን ይፀልያሉ እውነት ነው ። ነገርግን ይህ የሁሉም ወንድማዊ ሽክም እንጂ ለቅዱሳን መላዕክት ፣ ለማሪያም እና ለሰማዕታት ብቻ የተሰጠ ነገር አይደለም ።

3ኛ, ደግሞም በህይወት እስካሉ ድረስ ብቻ ነው ይህንን የሚያደርጉት ። ከሞቱ በኋላ የእነርሱ የምልጃ አገልግሎት እንደሚቀጥል የሚያመለክት አንድም የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባብ የለም ደግሞም እኛ ለእነርሱ እንድንፀልይ አንድም ትዕዛዝ አልተሰጠንም ።

በአካል አጠገባች ያሉትን ቅዱሳን ፀልዩልን የሚለውን መልዕክት በቀጥታ እንነግራቸዋለን ፣ በስልክም ልንነግራቸው እንችላለን ። ከእኛ በአካል ለተለዩ ቅዱሳን እንዴት አድርገን ነው የፀሎት ጥያቄአችንን ለእነርሱ የምናቀርበው ? እነርሱ እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ የመገኘት እና ሁሉን የማወቅ ባህሪ የላቸው ። ብዙዎች ለእዚህ ጥያቄ መልስ ስለሌላቸው የፀሎት ጥያቄአቸውን በፀሎት ነው በአካል ለተለዩን ቅዱሳን የሚያቀርቡት ። በእዚህም ፀሎት ተቀባይ አንዱ እግዚአብሔር ብቻ የመሆኑን እውነታ ይዘነጉታል ።

## ኢየሱስ ይማልዳል ፣ ታዲያ የኢየሱስ ክርስቶስ ምልጃ ጥቅሙ ምንድነው ?

**— ዕብራውያን 7፥25 (አዲሱ መ.ት) ። "ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁል ጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።"**

በቁጥር 24 ላይ ኢየሱስ ዘላለማዊ የማይሞት መሆኑን ከብሉይ ሊቀ ካህናት ጋር አነጻጽሮ ይነግረናል ። ኢየሱስ ዘላለማዊ መሆኑን መግለጽ ለምን አስፈለገ? ኢየሱስ ዘላለማዊ መሆኑን መግለፅ ያስፈለገው ለህዝቡ የሚሰጠው ጥቅም ለሁልጊዜ የማያቋርጥ ምልጃ ሊያቀርብላቸው ዝግጁ መሆኑ ለመግለጽ ነው ። ስለዚህ በእዚህ ቁጥር ግልጽ በሆነ መንገድ ኢየሱስ ይማልድልናል ። ዘላለማዊ መሆኑ ለእኛ የሚስገኘው ውጤት ምልጃው ነው ይለናል ።

የምልጃው ጥቁሙስ ምንድነው ?

ውጤቱ/ጥቅሙ ማዳን ነው ። ይህንን ከማብራራቴ በፊት የኢየሱስ የምልጃ አገልግሎት ከሌሎች ማላጆች የሚለይበት አንዱ ምክንያት የሚያድን ስለሆነ ነው ። ምክንያቱም ማዳን የእግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ። **— ዮናስ 2፥9 (አዲሱ መ.ት) ። ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።""** በተለይም ፦ **በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን** የሚለው አገላለፅ የኢየሱስ ምልጃን ለየት ያደርገዋል ። ወደእግዚአብሔር መድረሻው መንገድ ኢየሱስ ነው ። ወደእግዚአብሔር ያለ ኢየሱስ መድረስ አይቻልም ። መግቢያ በሩ አንድ ነው ፣ እውነት እና ህይወት መንገድ ኢየሱስ ብቻ ነው ።

**— የሚመጡትን**

እዚህ ጋር ኦርቶዶክሶች ኢየሱስ አስታራቂ ነው ብለው ይተረጉሙና ወደ እርሱ የሚመጡትን የሚለውን ደግሞ አማኞች ያልነበሩ ሰዎች ወደ እርሱ ሲመጡ ኢየሱስ ያስታርቃቸዋል ይላሉ ። ይህ ብቻ አይደለም የአተረጓጎም Inconsistency እንመለከታለን ። ስለ እነርሱ የሚለውን ስለ ካህናት ነው ይላሉ ። ይህ ትርጉም የማይሰጥ ነው ። የብሉይ ኪዳን ካህናት አሁን ላይ ከሌሉ ስለ እነርሱ መማለድ ትርጉሙ ምንድነው ? ደግሞም የሚያስታርቀው ብለው ከተረጎሙት የብሉይ ኪዳን ካህናት ከሞቱ በኋላ ምኑን ከምኑ ነው የሚያስታርቁት ? **— ዕብራውያን 9፥27 (አዲሱ መ.ት) ። "ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወስኖበታል።"**

የሚመጡትን የሚለው የግሪክ ቃል ፦ **ቶውስ ፕሮስኤርኮሜኑሴ** ነው የሚለው ። ይህ ቃል present participle

ነው ። ድርጊቱ ከበፊት ተነስቶ አሁንም የሚቀጥል መሆኑን የሚያሳይ ነው ። ማለትም ወንጌል ሰምተው አምነው የዳኑት በክህነቱ ያድናቸዋል ።

**– ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል**

ፈፅሞ የሚለው በሙላት የሚለውን ትርጉም ይሸከማል ፣ በሙላት ሊያድናቸው ይችላል ። ይህ ድነትን አሁን አግኝተዋል በሙላት ደግሞ ይህንን ድነት ያገኙታል እያለ ነው ። ልክ ምዕራፍ 4 ላይ ወደ እረፍቱ ገብተናል እረፍቱን ደግሞ በሙላት እንጠብቀዋለን እንደሚለው ማለት ነው ።

## ማጠቃለያ

ኢየሱስ አማላጅ ነው ስንል ተራ የሃይማኖት ክርክር እያወራን አይደለም ። መፅሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው ። መፅሐፍ ቅዱስ የተሸከመው የሃሳብ ክብደት እና የኢየሱስ ምልጃ ውጤት ድነት በመሆኑ ምክንያት አጥብቀን ልንይዘው የሚገባ እውነታ ነው ። ኢየሱስ እኛን ወክሎ በሰማይ አለ ፣ እኛ እሱን ወክለን በእዚህ በምድር አለን ። የቤተክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ራሱን ስለእኛ በአብ ፊት ሲያሳይ ፣ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን ራስ የሆነውን ክርስቶስ በምድር ትገልጣለች ። የተሳሰርንበት ኪዳን ፣ የተጋመድንበት ገመድ ለበጠስ በማችችል በክርስቶስ ፍቅር ነው ።

**ወንድም ተካልኝ ኃ/ሚካኤል**